May 9, 2022
ግንቦት 1፣ 2014 ዓ/ም

# በፋኖ ላይ መዝመት በአማራ ህልውና ላይ መዝመት ማለት ነው!

## ከአማራ ሕዝባዊ ኃይል ( ፋኖ ) የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ (ጋሻ አማራ) የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ

በቅርቡ በታሪካዊቷ ጎንደር ከተማ ለዘመናት ተከባብሮ በሚኖረው በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ማህበረሰብ የተፈጠረው ግጭት መነሻው የቀብር ድንጋይ ነው ብሎ መቀበል በስተጀርባ ሆነው ሴራውን ላቀነባበሩትና ጠቡን ለቆሰቆሱት ወንጀለኞች ሽፋን መስጠት ነው ብለን እናምናለን። በተለይም ባለፈው አራት ዓመታት ኢትዮጵያ ሰላም በተነሳችበት፣ ሚልዮኖች በተፈናቀሉበት፣ በመቶ ሺዎች ሕይወታቸውን ባጡበት፣ አማራው በቤኒሻንጉል-ጉሙዝና በኦሮሚ ያክልሎች በየጊዜው በማንነቱ በሚታረድበት፣በአማራና በአፋር ክልሎች ከተማዎች በተደመሰሱበትና፣ ከሁሉም በላይ ዶ/ር አብይ አህመድ የአማራ ሕዝባዊ ኃይልፋኖን ትጥቅ ለማስፈታትና ድራሹን ለማጥፋት እየተንቀሳቀሰ ባለበት ወቅት በጎንደር ላይ የተፈጠረውን ከቀብር ድንጋይ ጋር ማያያዝ ነገሩን ማቅለል ይመስለናል። የሀገር ሽማግሌውን ሸህ ከማል ለጋስን ለመቅበር በተሰበሰበው የሙስሊም ወገኖቻችን ላይ ቦንብ የወረወረው ግለሰብ ወይም ስብስብ ወንጀሉን የፈፀመው የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ተቆርቋሪ ስለሆነ ነው ብሎ መደምደም ከላይ የተጠቀሰውን የሃገራችንን ሁኔታ አለማገናዘብና ሴራውን ላቀነባበሩት ማምለጫ መንገድ መክፈት ይመስለናል። እውነቱን ተገንዝቦ የችግሩን መንሥኤ ፊትለፊት አለመጋፈጥ ማህበረሰቦቹን ለተከታታይ ጥቃት ማጋለጥ ነው ብለንም እናምናለን። በዚህ አጋጣሚ በሀገር አፍራሾች ደባ ምክንያት ለሞቱት ሙስሊምና ክርስቲያን ወገኖቻችን ቤተሰቦች መፅናናትን እንመኛለን።የሁለቱም የእምነት ተከታዮች የፈረሱትን መስጊዶች በጋራ እንዲሰሯቸውና ጠላትን እንዲያሳፍሩት እናሳስባለን።

ሀገር የማፍረስ ፕሮጀክት ያነገበ ጠ/ሚንስትር በሚመራት ሀገር ጎንደር በተፈፀመው አሳዛኝ ተግባር የሌሎቹ እጅ መኖሩ ሊደንቀን አይገባም።ነገሮች የተቀነባበሩ ስለሆነ ሁኔታውን የበለጠለ ማጦዝ አሰፍስፎ ይጠብቅ የነበረው የአህመዲን ጀበል ፅንፈኛ የሰለፊ ቡድን በወራቤ በርከት ያሉ ቤተክርስቲያናትን ሲያቃጥል ጊዜ አልፈጀበትም። እሳቱን ለማጥፋት የወጡ ሰዎችንም በመደብደብ የአካል ጉዳት አድርሷል። ይህ ቡድን ለአማራ ክልል እንግዳ አይደለም።አጣዬ በተደጋጋሚ ስትወረርና ስትወድም እንዲሁም ወራሪው ሕወሃት ደብረሲና ሲደርስ በማህበራዊ ሚድያ በደስታ ሲፈነድቅ ነበር።በኦሮሚያ ክልል ሙስሊም አማራዎች በማንነታቸው በየጊዜው ሲታረዱ አንድም ቀን ድምፁን አሰምቶ አያውቅም። ስለሆነም ይህ ቡድን ከጎንደር ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባና በደሴ በሚገኙት ጀሌዎቹ አማካይነት በምኑም ላይ በለለበት ፋኖ ላይ"ፋኖ አሸባሪ ነው"፣ "ፋኖ አክራሪ ክርስቲያን ነው" የሚል ዘመቻ መክፈቱ ሊደንቀን አይገባም። ለመሆኑ ፋኖን "አክራሪ ክርስቲያን" የሚለው በስሜን ወሎ ፀረ-ወያኔ ትግሉን የሚመሩትን እነ ፋኖ ጀነራል ሃሰን ከረሞን ሙስሊሞች አይደሉም እያለን ይሆን? የጀነራል አሳምነው ፅጌ ስም የተሰየመውን የፋኖ ብርጌድ አዛዥ የሆኑትን እነ መሬ ዎዳጆን ለማን አሳልፎ ሊሰጣቸው አስቦ ይሆን? የሕወሃትን ምሽግ ሲሰብሩ የተሰውትን እነፋኖ ሙሐምድ ደጉንና ሰይድ ገረየስን እናሌሎቹም በእምነታቸው የማይደራደሩ ሙስሊሞች እንደሆኑሊ ክደን ይሆን? ሃቁ ግን ከአብይ አህመድ ጀምሮ ጀዋር ሙሃመድ ከእሥር ከተፈታ ወዲህ የጠ/ሚንስትሩ ደጋፊ የሆነው ይህ ፅንፈኛ ቡድንና እንደ ኦፌኮ የመሰሉ ድርጅቶች የከነከናቸውና እንቅልፍ የነሳቸው ነገር ቢኖር ፋኖ የአማራው የጋራ እሴትና ሁሉን አቃፊ መሆኑ ነው። በፋኖ ውስጥ የነሱ ውድቀት ፍንትው ብሎም ስለሚታያቸው ነው።

አብይ አህመድ ከአማራ ሕዝብ አብራክ የወጣውንናለ አማራ ሕዝብ ህልውና ብሎም ለኢትዮጵያ እንደ ሃሀገር መቀጠል የቆመውን ፋኖን እንደ ዋና ጠላት አድርጎ ከቆጠረው ዋል አደር ብሏል። ጠ/ሚንስትሩ በሕወሃት ወረራ ጊዜ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለውን

ፋኖን ስንቅና ትጥቅ እንዳይደርሰውና በባዶ ሆዱና እግሩ እንዲዋጋ ያደረገውና ዛሬም የሚያሳድደው አገር የማፍረስ አጀንዳውን የሚገዳደርበት ብቸኛ ኃሃይል ስለሆነ ነው። ዛሬ ሕወሃት የፋኖን ያህል የአብይ አህመድ አጀንዳ አይደለም።ማስረጃውም ብርሃኑ ጁላን ሲሸልስ ድረስ ልኮ ከሕወሃቱ ጄነራል ታደሰ ወረደ ጋር ፋኖን በጋራ ስለማጥፋት ተደራድሯል።ስለዚህ ፋኖን ለመምታት መንደርደሪያ እንዲሆን የጎንደሩ ግጭት መቀነባበር ነበረበት። ዋና ተዋንያኖቹም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ባሕርዳርና ጎንደር የሚርመሰመሱት በተመስገን ጥሩነህ የሚመሩት የአብይ አህመድ ደህንነቶችና ሁኔታውን ያመቻቸላቸው ምን ጊዜም የወገኑ ጠላት የሆነው ብአዴን መሆናቸውን ሕዝቡ ሊያውቅ ይገባል እንላለን። ተጠያቂዎቹም ወንጀለኞቹም እነሱ ናቸው! ይህ መግለጫ እየወጣ ባለበት ሰዓት ደቡብ ወሎ ገራዶ የሚገኘውን የፋኖ ካምፕ አስከብቦታል። በሰሜን ወሎ ከሕወሃት ኃይል ጋር ለተፋጠጠው የፋኖ ኃይል ደጀን የነበረውን የአማራ ክልል ልዩ ኃሃይል አንስተውታል። ሴራውም ቀጥሏል።

ጀግናው የአማራ ሕዝብ ሆይ! ለሀገርህ ያለህ ክብርና ፍቅር ከስነ-ልቦናህ የማይፋቅ ስለሆነ ለማንም ጥያቄ እንዲያነሳበት አትፍቀድለት። ስለሆነም ዛሬ ያንተ ዋና አጀንዳ ህልውናህን ማስጠበቅ ብቻና ብቻ ነው። ዙሪያህን ሊያጠፉህ በሚፈልጉ ጠላቶች ተከበሃል። በተለይም ሕወሃትና የኦሮሞ ብልጽግና እየተናበቡ የሚያሳዩህ መከራ መቼም አያባራም። ጄኔራል ተፈራ ማሞን ከሥልጣኑ ካነሱት በኋላ የክልልህን ልዩ ኃይል እየበተኑብህ ነው። በህልውናህ ላይ የተቃጣብህን አደጋ ፈጽሞ ማጋነን አይቻልም። ስለሆነም ከልጅህ ከፋኖ ጎን ከመቼውም በበለጠ እንድትቆም ጥሪያችንን እናቀርብልሃለን። ዕድሜያቸውና አቅማቸው የሚፈቅድላቸውን ልጆችህን ፋኖን አንዲቀላቀሉ አድርግ። አንተም ራስህ ፋኖ ነህና በመንደርህ፣ በቀበሌህና በወንዝህ በጎበዝ አለቃ ተደራጅ። ነገር ግን ሁሉም አማራ አሁኑኑ በአንድነት ተደራጅቶ ህልወናውን ካላስጠበቀ በስተቀር “አማራ” የሚባል ሕዝብ እኮ እዚህ አካባቢ ይኖር ነበር የሚባልበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም። በቅርቡ የሚታየው የአማራን ልዩ ኃይል፣ የአማራ ሚሊሺያና ፋኖን ተሸላሚና ያልተሸለመ በሚል ጨዋታ የአማራውን የህልውና መከታ የሆኑትን የአማራ ኃይሎች በመከፋፈል የሚደረግ የብአዴን / ብልጽግና ሌላ ዙር ሴራን በመገንዘብ ማክሸፍ ይገባል። ለፋኖ፣ ለአማራን ልዩ ኃይል፣ ለአማራ ሚሊሺያና ሽልማታቸው የአማራን ህልውና በማስከበርና ሀገራቸውን በመታደግ የገቡበትን ታሪካዊ ትግል በድል በመወጣት ነው። አማራን በመላው ሀገሪቱ የአሰቃቂ ወንጀሎች ሰለባ ተደርጎ እረፍት አልባ ህይወት እንዲመራ ቀንና ሌሊት የሚሰራው የአብይ አህመድ የብልጽግና አገዛዝ ከአማራ አብራክ ለወጡ ኃይሎች ወዳጅ ወይም ሸላሚ ለመሆን መቅረብ ትልቅ ቧልትና አይን አውጣነት መሆኑን ያለፉት አራት የነውጥና የመንግስታዊ ውሸት አመታት ምስክሮች ናቸው። አማራ ወገናችን በያለህበት የህልውናህ መከበር ዋስትና የሆነውን ፋኖን እንደ አይንህ ብሌን በመጠበቅ በጣምራ ወረራ ዋጋ ያስከፈለህን የብልጽግና አገዛዝ ህዝብን ለህዝብ ሰላም የማይዘራን ጦርና ሕግ ተጠቅሞ ፋኖን ትጥቅ የማስፈታት ሴራ በአንድነት ቆመህ ማክሸፍ ምርጫህ ሳይሆን ግዴታህ መሆኑን እናስገነዝብሀለን።

ጀግናው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በያለህበት! ዛሬ አማራ ላይ በማንነቱ የሚፈጸምበት ወንጀል ነገ ያንተ ዕጣ ፋንታ እንደሚሆን አትጠራጠር። ውድ ኢትዮጵያ ሃሀገራችንን በማፈራረስ ላይ ያለው የኦሮሞ ብልጽግና አንተንም በተወሰነ ደረጃ እየጎሸመህ እንደሆነ መካድ አይቻልም። ሥልጣን እስካልተቀናቀንኩት ድረስ አያስጋኝም ብለህ አትዘናጋ። ዛሬ የኦሮሞ ብልጽግናና አጋሮቹ ሥልጣኑንም፣ ሥራውንም፣ ባንኩንም፣ ታንኩንም ስለተቆጣጠሩት ልጆችህ የከፋ እንጂ ብሩህ ነገ አይጠብቃቸውም። ነጋ ጠባ አጀንዳ የሚሰጡህ ያለ ምክንያት አይደለም። ግባቸውን ለመምታት በዘር ብቻ ሳይሆን በሃይማኖትም እያጋጩህ ነው። ስለሆነም ሀገራችን ኢትዮጵያንና ወገናችንን በጋራ ለመታደግ በዚህ 81ኛው የአርበኞች የድል በዓል በተከበረበት ሰሞን ከፋኖና ከአማራ ወገን ህጎን እንድትቆም ጥሪያችንን እናቀርብልሃለን!!!

የአማራ ህልውና በልጁ በፋኖ ይከበራል!
ኢትዮጵያን ለጎጠኞች እንዳትመኝ እናደርጋታለን!

ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ/ም
ጋሻ አማራ